

አሁን አሁን ላይ ከማያቸው ወንድሞች ውስጥ (ዕቅበተ እምነት ላይ የሚሳተፉ) አብዛኞቹ ዘንድ ያልተስተዋለ ችግር እና ምናልባት ዝም ከተባለ ወደፊት እንደትልቅ ገደል መሃላችን የሚቆም የእቅበት መንገድ ልዩነት አለ ። አንዳንዶች ለታላቁ የመካከለኛ ዘመን ክርስትያን ፈላስፋ አኳይነስ እና ተፈጥሯዊ ነገረ መለኮት[1] ልዩ ፍቅር ያሳያሉ አንዳንዶች ደግሞ በጣም ፀረ ምዕራባዊ (anti western) ሆነው ተፈጥሯዊ ነገረ መለኮት ላይ ብዙ ያልተገባ ትችት ያሰሙና በተቃራኒው ብቸኛው ተገቢ የፍልስፍና አካሄድ ፕረሰፖዚሽናሊዝም ነው ሲሉ ይናገራሉ ።

ተፈጥሯዊ ነገረ መለኮት የምንለው አፅናፈ ዓለምን በመመልከት ከእምነት እገዛ ውጪ በአመክንዮ ስለእግዚአብሔር የሚያጠናን የነገረ መለኮት ክፍል ነው ። ከእምነት እገዛ ውጪ ማለት እንደ ቅዱሳት መፃህፍት ያሉትን የቅዱስ አስተርእዮን ይዘት በማስረጃነት ሳይጠቀም የሃይማኖትን እውነታ ያረጋግጣል ማለት ነው ። እንደሚታወቀው ሁለት አይነት አስተርእዮዎች አሉ ኩላዊ (General Revelation) እና ቅዱስ (Specific Revelation) ናቸው ። ስለዚህም ተፈጥሯዊ ነገረ መለኮት የምንለው በአጭሩ ስናጠቃልለው ያለ ቅዱስ አስተርእዮ በኩላዊው አስተርእዮ ይልቁኑም በአመክንዮ ስለ እግዚአብሔር የሚያጠናን የነገረ መለኮት ክፍል ነው ። እንደነ Thomas Aquinas ፣ Richard Swinburne እና William Lane Craig የመሳሰሉት በተፈጥሯዊው ነገረ መለኮት ዘርፍ የሚታወቁ ፈላስፋዎች ናቸው ።

Presuppositionalism ደግሞ የሃይማኖትን እውነት ግሉል ከሆነ አመክንዮ ከማሳየት ይልቅ ከራሱ ከክርስትና እይታ በመነሳት ክርስትና እውነት እንደሆነ ማሳየት ነው ። በክርስትና እይታ ካልሆነ በስተቀር አመክንዮ ፣ ግብረ ገብነት ፣ ስምምነት ፣ ውበት እነዚህን የመሳሰሉ ለህልውናም ሆነ ለእውቀት መሠረታዊ ነገሮች ትርጉም የለሾች ናቸው ። ኢአማንያንን ጨምሮ ሁሉም ሰው እውነት መሆናቸውን የሚያምኗቸው መሠረተ ሀሳቦች እንዲሁም የሌሎችን ነገሮች እውነታ ለማሳየት የሚጠቀሙባቸው ሀሳቦች በክርስትና አስተሳሰብ (Phronema) ብቻ እውነት የሚሆኑ ናቸው የሚል ነው ።

እነዚህ ከላይ የጠቀስኳቸው ትርጓሜዎች ላይ ብዙ ማብራሪያ መጨመር ይቻላል ። ሁለቱም የክርስቲያን ፍልስፍና መንገዶች የየራሳቸው የሆነ መልካም ጎን እና ደካማ ጎን አላቸው ። ከአካይነስ አርስቶትላዊ አመክንዮ በመጀመር በሁለቱም ላይ ያለኝን አስተያየት በተለያየ ጽሁፍ አስቀምጣለሁ፡

[1] Natural Theology

## <u>የአኳይነስ አርስቶትላዊ አመክንዮ</u>

ቶሚስት ፈላስፋ Edward Feser ይበልጥ ግልጽ አድርጎ የአኳይነስን አርስቶትላዊ አመክንዮ እንደሚከተለው በጥቅሉ ያቀርበዋል ፡

> "አንዳንድ ነገሮች በለውጥ ውስጥ እንዳሉ" ከተሞክሮ እናውቃለን ። ለውጥ ማለት ደግሞ የአንድ ነገር ከክሂል ወደ እውን መምጣት ነው ። ነገር ግን ማንኛውም ነገር ከክሂል ወደ እውንነት የሚመጣው በእውንነት ከዊን ውስጥ ባለ ነገር ብቻ ነው ፤ ለምሳሌ እሳት በእውን ያቃጥላል ፤ በክሂል ሙቀት ያለውን ባይነድ የማያቃጥለውን እንጨት በእውንም የሚያቃጥል እንዲሆን ያደርጋል ። እንዲሁም ማንኛውም ነገር በተመሳሳይ ጊዜ እና መልኩ የሚለ'ወጥም የሚለውጥም ሊሆን አይችልም ። ስለዚህም "በለውጥ ውስጥ ያለ ነገር ሁሉ በሌላ ነገር የሚለወጥ ነው" ይህንን ተከትሎ ሌላን ነገር የሚለውጥ አካል እራሱም በለውጥ ውስጥ ከሆነ የሚለውጠው ሌላ አካል መኖር አለበት ፤ እያለ ይቀጥላል ። ይህ ቅደም ተከተል እልቆ ቢስ ቢሆን ቀዳማዊ ጥንት ባልኖረ ነበር ፤ ልክ በትር የሚንቀሳቀሰው እጅ ስለሚያንቀሳቅሰው እንደሆነው ሁሉ በቅደም ተከተሉ ውስጥ ተከታይ አካላት የሚንቀሳቀሱት ቀዳማዊ ጥንት ስለሚያንቀሳቅሳቸው ብቻ ነውና ቀዳማዊ ጥንት ከሌለ ሌሎች የሚለወጡ አካላት ባልኖሩ ነበር ። ስለዚህ "በሌላ የማይለወጥ ቀዳማዊ ጥንት ላይ መድረስ ግድ ይላል ይህም ደግሞ እግዚአብሔር መሆኑን ሁሉ ይረዳል "[2]

---

[2] We know from experience that "some things are in motion" ("motion" in the Aristotelian sense just being change, as we saw in our discussion of Aristotle's reply to Parmenides). Now motion or change is just the reduction of something from potentiality to actuality. But "nothing can be reduced from potentiality to actuality except by something in a state of actuality" (ST I.2.3); for instance, fire, which is actually hot, makes wood, which is otherwise only potentially hot, become actually hot. Moreover, nothing can be both potential and actual in the same respect at the same time; what is actually hot, for example, is not at the same time potentially hot, but potentially cold. In that case, though, it is impossible for anything to be at the same time and in the same respect both that which is moved or changed and that which does the moving or changing. Hence, "whatever is in motion must be put in motion by another" (ST I.2.3). By the same token, if that which puts something else in motion is itself moving, there must be yet something further moving it, and so on. But if such a series went on to infinity, then there would be no first mover; and if there were no first mover, there would be no other movers, for "subsequent movers move only inasmuch as they are put in motion by the first mover; as the staff moves only because it is put in motion by the hand" (ST I.2.3). It follows that "it is necessary to arrive at a first mover, put in motion by no other; and this everyone understands to be God" (ST I.2.3).

በዚህ መልኩ ከተቀመጠው የአኳይነስ ሙግት[3] የምንረዳው አመክንዮውን የሚጀመረው ለ ለውጥ ትርጉም በማስቀመጥ እንደሆነ ነው ።

ለውጥ ፡ የአንድ ነገር ከክሂላዊ ኩነት ወደ እውናዊ ኩነት መምጣት ነው ።

ይህንን ተከትሎ የመጀመርያው ሒስ የዚህ ትርጓሜ ክበባዊ መሆን ነው ። ብያኔው ለውጥን የሚያብራራው "ከክሂል ኩነት ወደ እውንነት ኩነት መምጣት" በሚል ሲሆን ይህ ማለት ደግሞ በክሂል ኩነት ሲኖር የነበረን ህልውና ወደ እውንነት ኩነት መቀየር ማለት ነው ማለትም ከአንድ ኩነት ወደ ሌላ ኩነት ተለውጧል ። "መለወጥ" ሊበየን የሚገባው ሀሳብ ሆኖ ሳለ አኳይነስ ግን ሊተረጎም የሚገባውን ሀሳብ በመጠቀም እራሱኑ ሀሳቡን በመተርጎም ክበባዊ የሆነ ትርጓሜ ይሰጣል ።

ሲቀጥል "የክሂል እውን መሆን" የሚለው የለውጥ ሐተታ ፤ በሁሉት ተከታታይ የጊዜ ቅጽበቶች መካከል የተለያየ ጠባይን የሚይዝ አንድ ጽኑ አካል መኖሩን መሠረተ ሀሳብ አድርጎ የያዘ ይመስላል ። አንድ ጽኑ አካል በ ሆነ ጊዜ t1 "P" የሚባልን ጠባይ ክሂል አድርጎ ይይዛል ፤ በሌላ ጊዜ t2 ደግሞ Pን እውን ጠባይ አድርጎ ይይዛል ። ስለዚህ አካይነስ ለውጥ እንዲኖር ለውጥን የሚያስተናግድ መሠረታዊ ህላዌ(grounding substance) መኖሩን መሠረተ ሀሳብ ያደረገ የለውጥ ሐተታን ይጠቀማል ። ችግሩ ግን ይህን መሠረተ ሀሳብ እንዲሁ የሚቀበል የትኛውም እሳቤ እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ(creation ex nihilo) የሆነውን የዓለምን መፈጠር እንደ ለውጥ አይቆጥረውም ፤ ምክንያቱም የዓለም ፍጥረት ያልነበረ ሐላዌ ወደ ህልውና መምጣት ነውና ለውጥን የሚያስተናግድ grounding substance የለውም ። በመሆኑ ይህ ሐተታ ጠባብ[4] በመሆን ይተቻል ።

---

[3] አካይነስ ሙግት እራሱ ጠቅልሎ እንደፃፈው ፡ The first and more manifest way is the argument from motion. It is certain, and evident to our senses, that in the world some things are in motion. Now whatever is in motion is put in motion by another, for nothing can be in motion except it is in potentiality to that towards which it is in motion; whereas a thing moves inasmuch as it is in act. For motion is nothing else than the reduction of something from potentiality to actuality.1 But nothing can be reduced from potentiality to actuality, except by something in a state of actuality. Thus that which is actually hot, as fire, makes wood, which is potentially hot, to be actually hot, and thereby moves and changes it. Now it is not possible that the same thing should be at once in actuality and potentiality in the same respect, but only in different respects. For what is actually hot cannot simultaneously be potentially hot; but it is simultaneously potentially cold. It is therefore impossible that in the same respect and in the same way a thing should be both mover and moved, i.e., that it should move itself. Therefore, whatever is in motion must be put in motion by another. If that by which it is put in motion be itself put in motion, then this also must needs be put in motion by another, and that by another again. But this cannot go on to infinity, because then there would be no first mover, and, consequently, no other mover; seeing that subsequent movers move only inasmuch as they are put in motion by the first mover; as the staff moves only because it is put in motion by the hand. Therefore it is necessary to arrive at a first mover, put in motion by no other; and this everyone understands to be God.

[4] Narrow Definition

## የሚለወጥ ሁሉ በሌላ የሚለወጥ ነው

አኳይነስ ክሂል በእራሱ እውን የሚሆን ሳይሆን ቀድሞውኑ እውን በሆነ በሌላ ነገር ብቻ ወደ እውንነት የሚመጣ ነው ይላል ። ቀድሞውኑ እውን በሆነ በሌላ ነገር ነው እውን ማድረግ የሚቻለው ለሚለው ግን ምንም አመክንዮ አላቀረበም ።

P2 : "የሚለወጥ ሁሉ በሌላ የሚለወጥ ነው"
ምክንያት : "ክሂል እራሱን በእራሱ ስለማይለውጥ "

ማለትም "ክሂል እውን የሚሆነው እውን በሆነ ሌላ ነገር ነው" ለሚለው የቀረበው ምክንያት "ክሂል እራሱን በእራሱ ስለማይለውጥ" የሚል ነው ። ይሄ ደግሞ እራሱኑ መጀመርያ የተናገረውን ቃላት ብቻ ለውጦ መልሶ መድገም Begging the Question fallacy ነው ። እንደገናም አብዛኛው ሰው እንደሚያምነው በሆነ መልኩ አስገኚ የሌላቸው self-moving የሆኑ ተወስነው ያልተገኙ እንደ ነፃ ፈቃድ ያሉ ግብራት አሉ : እነዚህ

1. በሆነ መልኩ ያልተገኙ ናቸው ።
2. በሆነ መልኩ ግን ከአእምሮ የተገኙ ናቸው ።

የአካይነስ የመንስኤያት እሳቤን ወደ ሰው ልጅ ፈቃድ እና አእምሮ የምናመጣው ከሆነ ፤ በአእምሮ ውስጥ ያሉት መስተጋብሮች ግብራቶቻችን ሁሉ የሚወስኑ efficient causes ይሆናሉ ። ይህ ደግሞ ወደ neurochemical determinism ያመራናል ።

ወደ ሦስተኛው ሀሳብ ስናመራ :
P3 : የክሂል እውን መሆን ቅደም ተከተል እልቆ ቢስ ሆኖ ሊቀጥል አይችልም ።
አካይናስ ሁለት አይነት መንስኤያዊ ቅደም ተከተሎችን ይለያል :

1. Per se
   በእንዲህ ዓይነቱ ቅደም ተከተል ውስጥ እያንዳንዱ አካል ግብሩን ወይም አስገኚቱን የሚያገኘው በዚያው ቅጽበት ከቀደመው ካስገኘው አካል ነው ። ለምሳሌ "በትርን በመጠቀም ድንጋይ የሚያንቀሳቅ እጅን" ብንወስድ የድንጋዩን እንቅስቃሴ በዛው ቅጽበት ያስገኘው የበትሩ እንቅስቃሴ ሲሆን የበትሩም እንቅስቃሴ በዚያው ቅጽበት የተገኘው ከእጁ እንቅስቃሴ ነው ። እጁ የማይንቀሳቀስ ቢሆን በትሩ ባልተንቀሳቀሰ በትሩም ስላልተንቀሳቀሰ ድንጋዩ ባልተንቀሳቀሰ ነበር ። በዚህ ቅደም ተከትል ውስጥ ተከታይ አካላት በሙሉ ሚንቀሳቀሱት እጁ ስለሚንቀሳቀስ ነው ። ይህ ደግሞ እንዲህ ባለው ቅደም ተከተል ቀዳማዊ አካል ባይኖር ሌሎቹ እንደማይንቀሳቀሱ ያሳያል ። ስለዚህ ቅደም ተከተሉ እልቆ ቢስ ሆኖ ሚቀጥል ሳይሆን ሚያንቀሳቅሰው

በማያስፈልገው አካል የሚፈጸም ቅደም ተከተል ነው ።

2. Per accidents
   እንዲህ ባለው ቅደም ተከተል ውስጥ የቀደሙት አስገኚዎች ለሚከተሉት አስገኚዎች ግብር መጽናት አስፈላጊ አይደሉም ። ለምሳሌ ፡
   አያት የአባትን ህልውና አባት ደግሞ የልጅን ህልውና ሲያስገኝ አያት አባት እና ልጅ ከተገኙ በኋላ ባይኖር ከእርሱ በኋላ ያሉት አባት እና ልጅ ህልውናቸው ይቋረጣል ማለት አይደለም ።

Per se በሆነው ቅደም ተከተል ከቀዳማዊው አስገኚ ውጪ ያሉት አካላት በሙሉ ለቀዳማዊው አካል እንደ ነዋያት ናቸው ፤ እስከ ቅደምተከተሉ መጨረሻ ድረስ ያለው ውጤት ከቀዳማዊው አካል ተገኝቶ በሌሎች አስገኚዎች በኩል የሚፈጸም ነው ልክ እጅ በበትር አማካኝነት ድንጋይ እንደሚያንቀሳቅስ ። በዚህ ምሳሌ ውስጥ በትር በእራሱ ድንጋይን አላንቀሳቀሰም ድንጋይም በእራሱ አልተንቀሳቀሰም ፤ በትሩ እጅ ስላንቀሳቀሰው ተንቀሳቀሰ እንጂ ። እጅ ባይኖር ኖሮ ደግሞ ድንጋዩም ባልተንቀሳቀሰ ነበር ። ስለዚህ በእራሱ ኃይል ያለው ቀዳማዊ ጥንት እንዲህ ባለው ቅደም ተከተል ውስጥ ይገኛል ማለት ነው ። ስለዚህ ቅደም ተከተሉ እልቆ ቢስ አይደለም ለሚለው የአኳይነስ ምክንያት ይህ ነው ፡

አሁንም ይህ አመክንዮ በምክንያት ያልተደገፉ ሀሳቦችን የያዘ ነው ። "በእራሱ ኃይል ያለው ቀዳማዊ ጥንት ከሌለ መላው ቅደም ተከተሉ ባልኖረ ነበር " የሚለውን ሀሳብ በእራሱ እሙን እንደሆነ ምንም ድጋፍ እንደማያስፈልገው አድርጎ ያለማስረጃ ይተወዋል ።

## እልቆቢስ ቅደም ተከተል ላለመኖሩ

ምንም እንኳን አኳይናስ ለአመክንዮው ያቀረበው የለውጥ ሐተታ ክበባዊ እና ጠባብ ቢሆንም ፣ ክሂል እውን እንዲሆን ሌላ እውን የሆነ ነገር ማስፈለጉን ባያሳይም  እንዲሁም እልቆ ቢስ ቅድም ተከተል ለምን እንደማይኖር ምክንያቱን በግልጽ ባያስቀምጥም ። በሁሉም ነገር ግን ተሳስቷል ማለት አይደለም ፤ አኳይነስ ማስረጃ ባለማሳየቱ የርቱዕነት ጥያቄ ቢኖርበት እልቆቢስ ቅደም ተከተል የለም በሚለው ሀሳብ ስህተት ነው ማለት አይደለም ። እልቆቢስ ቅደመ ተከተል ላለመኖሩ ብዙ ማስረጃዎችን ማሳየት ይቻላል ፣ ለምሳሌ ሒሳብን በመጠቀም አንዱን ለመመልከት ያህል ፡

Let S = 1+2+3+4 …
S = 1 + (2 + 3 + 4) + (5 + 6 + 7) + (8 + 9 + 10) …
S = 1 + 9 + 18 + 27 + 36 …

$S = 1 + 9 (1 + 2 + 3 + 4 \ldots)$ , but $(1 + 2 + 3 \ldots) = S$
$S = 1 + 9 S$
$S - 9S = 1$
$-8S = 1$
$S = - \frac{1}{8}$

1. ህልው የሆነ ነገር በሙሉ ያለ Contradiction መሆን አለበት
2. እውን እልቆቢስ ቅደም ተከተል እንደ complete total ስንወስደው contradiction ያመጣል ። (contradictory የሆነው የአዎንታዊ ቁጥሮች ድምር አሉታዊ ቁጥር መምጣቱ ነው)
3. ይህ ሒሳባዊ እውነታ በምን መልኩ በህላዌያዊ ቅደም ተከተል ላይ እንደማይውል ርቱዕ ምክንያት ካልቀረበልን በቀር በህልውና የሚኖሩም እልቆቢስ ቅደም ተከተሎች እንዲህ ናቸው ብሎ መውሰዱ የሚገባ ነው ።

   C : ስለዚህ በህልውና እውን እልቆቢስ ቅደም ተከተል ሊኖር አይችልም ።

## ADS

ከአኳይነስ አምስቱ መንገዶች የመጀመርያዎቹ ሶስቱ ተመሳሳይ መዋቅር አላቸው ፡

- በሁለት ነገሮች X እና Y መካከል R ትሥሥር ይኖራል ።
- R irreflexive ነው ። ማለትም ማንኛውም ነገር ከእራሱ ጋር R ትሥሥር ሊኖረው አይችልም ።
- R transitive ነው ። ማለትም A ከB ጋር R ትሥሥር ካለው እና B ደግሞ ከ C ጋር R ትሥሥር ካለው  Aም በተዘዋዋሪ  ከC ጋር R ትሥሥር ይኖረዋል
- መጀመርያ የሌለው R ትሥሥር ያላቸው ነገሮች ቅደም ተከተል ሊኖር አይችልም ።

ስለዚህ ፡ ሌሎች ነገሮች በ R ትሥሥር የሚተሳሰሩት እርሱ ግን ከማንም ጋር R ትሥሥር የሌለው አንድ ልዩ ነገር ይገኛል ማለት ነው ።

የመጀመርያው አርስቶትላዊ አመክንዮ በ ክሂል እውን የመሆን ሂደት ይህንን መዋቅር ይከተለዋል ። R፡ actualization of Potential ነው ። ምንም ነገር የራሱን ክሂል እውን ማድረግ አይችልም ስለዚህ በራሱ ሳይሆን በሌላ እውን የሚሆን ነው ። በአጭሩ የሚኖረው የactualizers ቅደም ተከተል መጨረሻ ላይ ምንም ክሂል በሌለው ፍጹም እውን በሆነ(actus purus) አካል ይቋጫል እርሱም እግዚአብሔር ነው ። እግዚአብሔር actus purus ነው ከሚለው ተነስተን absolute divine simplicity(ADS) የሚባል ሀሳብ ላይ እንደርሳለን ።

actus purus ሲብራራ ፡
- እግዚአብሔር ምንም ክሂል የለውም
- በእግዚአብሔር ዘንድ ያለ ነገር በሙሉ ፍጹም እውን ነው ።
- ውላጤ ፣ ክሂል ፣ መጨመር ፣ መቀነስ የለበትም ።
- የክሂላዊ ኩነት እና እውናዊ ኩነት ውቅር አይደለም ።
- ፈጽሞ የሆነ እንጂ ሊሆን የሚችል ምንም የለበትም ።

ADS ደግሞ ፡
- በእግዚአብሔር ዘንድ ምንም real የሆነ ልዩነት የለም ፡
    - በባህርይው እና በህልውናው መካከል ልዩነት የለም
    - በባህርይው እና በጠባያቱ መካከል ልዩነት የለም
    - በፈቃዱ እና በእውቀቱ መካከል ልዩነት የለም
    - በባህርይው እና በግብራቱ መካከል ምንም ልዩነት የለም

እግዚአብሔር ፈጽሞ እውን ብቻ ነው ማለት ከግብራዊ ክሂል በቀር በእርሱ ዘንድ ምንም ክሂል የለም ማለት ነው ። real ልዩነት በእግዚአብሔር ዘንድ ካለ ደግሞ አንዱ ክፍል ያለ ሌላው ክፍል ሊኖር እንደሚችል ጠቋሚ ነው ፤ ስለዚህ አንድ ይሆኑ ዘንድ የአንድነት ክሂላቸው በሌላ እውን የሆኑ ናቸው ማለት ነው ። ስለዚህ ምንም ክሂል በእርሱ ዘንድ እንዳይኖር ምንም real distinction ሊኖር አይገባም ። እግዚአብሔር actus purus ከሆነ ምንም real ልዩነት በእርሱ ዘንድ አይኖርምና absolutely simple ነው ማለት ነው ።

በድጋሚ ለመግለጽ ፡ ማንኛውም really ውቅር አካል X፡ የተለያዩ ክፍላት A እና B እንዲሁም ሁለቱን የሚያዋህድ U አለው ፡ X = U(A,B) ነው ። ሁለቱን ክፍላት የሚያዋህድ U ከሆነ ከA እና B ተዋህዶ የተዋቀረው የX ህልውና በU አዋህጃነት ላይ የተመሰረተ ነው ። ስለዚህም X እውን የሆነ የመዋህድ ክሂል ይኖረዋል ማለት ነው ። X ምንም ክሂል የሌለው እንዲሆን ምንም real ልዩነት በእርሱ ዘንድ መኖር የለበትም ። እግዚአብሔርም እንዲሁ ያለ ምንም ክሂል ስለሆነ በእርሱ ዘንድ ምንም አይነት real ልዩነትም የለም ። ስለዚህ እግዚአብሔር በቶሚስቶች ዘንድ actus purus እና absolutely simple ነው ።

## Modal Collapse

1. በቶሚስት እሳቤ እግዚአብሔር actus purus እና absolutely simple ነው ።
2. እግዚአብሔር absolutely simple ከሆነ የእግዚአብሔር ባህርይው ፣ ህልውና ፣ ግብሩ ፣ ፈቃዱ ፈጽመው አንድ(identical) ናቸው ።

3. እግዚአብሔር ሊሆን በሚችሉት ዓለማተ ከዊን ሁሉ የሚገኝ Necessary ህላዌ ነው ።
4. የእግዚአብሔር ፈቃዱ እና ግብሩ ከእግዚአብሔር ባህርይ ጋር አንድ ከሆኑ ፤ ፈቃዱ እና ግብሩም ጭምር Necessary ናቸው ማለት ነው ።
5. እግዚአብሔር የመፍጠር ግብሩ Necessary ከሆነ ፍጥረትም Necessary ይሆናል ፡
6. ስለዚህ እግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን የ ፍጥረትም ህልውናም ጭምር Necessary ይሆናል ።

እግዚአብሔር absolutely simple ቢሆን ኖሮ ሁሉ ህላዌ የግድ ህልው የሚሆን ይሆናል ። ላይኖር የሚችል ምንም ነገር አይኖርም ነበር ። በድጋሚ የእግዚአብሔር ባህርይው ከፈቃዱ እና ከግብሩ ጋር ፈጽሞ አንድ ከሆነ ባህርይው ሳይለወጥ ፈቃዱ ሊለወጥ አይችልም ። የእግዚአብሔር ባህርይ ግን የማይለወጥ ስለሆነ ፈቃዱም እንዲሁ አይለወጥም ። ይህ ማለት እግዚአብሔር አለመፍጥር አይችልም አልያም ደግሞ አሁን ፈቅዶ ከፈጠረው ዓለም ሌላ ዓይነት ዓለም ሊፈጥር አይችልም ነበር ማለት ነው ።

በአጭሩ ይህ ማለት እግዚአብሔር ያለ መፍጠር ወይም ሌላ የመፍጠር ነፃነት የለውም ማለት ነው ።